

# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

# Ethiopian Civil Service University

## International and Public Relations Coordination Directorate

**Monthly Newsletter | September 2017 | Vol. 14 No. 2**

## IN THIS ISSUE


ECSU and MoND Sign MOU 1

Annual Plan Performance Evaluation Held 1

TCSCD Organizes Training 2

Gender and HIV/AIDS Affairs Directorate Gives Training 2

EKI Hailed ECSU 3

ECSU Holds Community Service Consultation 4

የግንባር ቀደሞች እውቅና 5



Tel. 0116 46 2887
P.O.Box 5648
E-mail: ecsupro@ecsu.edu.et
Website: www.ecsu.edu.et
FM Radio: 100.5 MHz


### ECSU AND MOND SIGN MOU

Ethiopian Civil Service University and Ministry of National Defense signed MoU to train the Ethiopian National Defense Force executive staff in Leadership and Good Governance in master's program on September 25, 2017 at ECSU Senate Hall.



### EKI Hailed ECSU

Ethiopian Kaizen Institute awarded Ethiopian Civil Service University two teams and three best performing individuals for their excelled performance in implementation of kaizen philosophy in their respective directorate on October7, 2017 at Ghion Hotel.



### የግንባር ቀደሞች እውቅና

የመጀመሪያና በበጀት ዓመቱ ብቸኛ የዋንጫ ተሸላሚ የሆኑት የስልጠና ፋሲሊቲና መስተንግዶ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሆኑት አቶ ሸሪፍ ሙዘይን ናቸው፡፡



## Our Vision

To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country

## ራዕያችን

የሀገራችንን ልማትና ትራንስፎርሜሽን እውን ለማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ፐብሊክ ሰርቪስ ከመገንባት አኳያ በ 2017 በአፍሪካ የልህቀት ማዕከል መሆን

## Our Mission

Enhancing the service orientation, transparency and accountablity of the public service by building its capacity through Specialized Education, Training, Consultancy, Research and Community Services.

## ተልዕኳችን

ፐብሊክ ሰርቪሱ የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሰ እና በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚሰራ እንዲሆን አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣ በስልጠና፣ በማማከር፣በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት

## Our Values

- Customer Focus
- Commitment
- Continuous Learning
- Welcoming Diversity
- Attention to the Disadvantaged
- Participatory Leadership
- Collaboration

## እሴቶቻችን

- ተገልጋይ ተኮር
- ቁርጠኝነት
- ሁሌም መማር
- ብዝሀነት መቀበል
- ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ
- አሳታፊነት
- ተባብሮ መስራት

# ECSU AND MOND SIGN MOU

Ethiopian Civil Service University and Ministry of National Defense signed MoU to train the Ethiopian National Defense Force executive staff in Leadership and Good Governance in master's program on September 25, 2017 at ECSU Senate Hall. The agreement was signed to deliver a Master's program for 48 executive staff recruited from the Ethiopian Air Force headquarters and executive staff of National Defense Force on an existing curriculum in Leadership and Good Governance through block-based face to face program.

In the signing ceremony Ethiopian Civil Service University President, Professor Fikre Dessalegn expressed his pleasure and mentioned ECSU's readiness to avail all the necessary facilities for the teaching learning activities. He also mentioned that ECSU has finalized the preparation and is waiting for the candidates to join the university. "With regard to the entrance examination we believe that it will be prepared to assess whether the candidates are equipped with the basic knowledge that a leader should acquire. College of Leadership and Governance has rich experience in producing all rounded and skilled leaders. It has taught for many years and contributed in filling

the gaps in the executive branch of the government. With this rich experience we believe the candidates from the Ethiopian National Defense Force will acquire a full- fledge skills and knowledge," professor Fikre added.



Colonel Bereket Wolde Abiyezgi Head of Defense Human Resource Management Main Department Office on his part expressed his pleasure in signing the agreement with ECSU. He also mentioned MoND is working hard to build the capacity of the Executive Staff with the modern leadership knowledge. In this regard, this agreement will help us to make our effort to be more effective, Colonel Bereket added.

It was learnt that based on the MoU signed between ECSU and MoND in 2011, Ethiopian Civil Service University has graduated 36 staff of MoND in leadership and good governance. It also provides post graduate class for the Ethiopian National Defense Force staff in three different cities Mekele, Shire and Harar without affecting the day to day operation .

# Annual Plan Performance Evaluation Held



Ethiopian Civil Service University community held one day discussion on the accomplishment of 2009 academic year plan and approval of 2010 E.C annual plan on 18th September, 2017 at Abay Hall. All academic and administrative staff participated in the discussion.

On his opening speech, Professor Fikre Dessalegn, Ethiopian Civil Service University president, welcomed the university's community and said besides its mandates of building the capacity of the public sector, ECSU has contributed a lot in structural improvement and the service delivery activities on different institutions by conducting problem solving researches and consultancy service. The university has prepared a five years strategic plan and executed different activities in 2009 E.C annual plan, Professor Fikre said.

He also mentioned that by the year 2009 the university has been engaged in restructuring both the academic and administrative wings, building the capacity of the staff and middle level managers, adopting different policies and guidelines. It has also registered great results at different levels and graduated a total of 1585 students. He thanked the university community for the achievements gained and requested them to work hard with the same spirit for a better performance in the next academic year.

On the program the University's 2009 E.C annual work performance report and the draft 2010 E.C academic year work plan were presented to the participants by the President's Office Director and Institutional Planning and Assessment Director respec-

tively and the participants have thoroughly discussed and commented on both reports.

Finally Reform and Good Governance Coordination Directorate presented the best performing workers and directors of the year 2009E.C and recognition and acknowledgement have been given for their outstanding efforts and motivations.



## TCSCD Organizes Training

Ethiopian Civil Service University Training and Consultancy Service Coordination Directorate organized three days training for Training and Consultancy Service wing directors and consultants on training design and methodology from September 10 to 12, 2017 at Training Center.



The training was given in two phases; Training Material Design and Development presented by Ato Alemayehu Seberu and Training Delivery Method; presented by Ato Tamru Geleta.
Asked about the objectives of the training W/ro Kumnegr Fikre, Director for Consultancy Service Coordination Directorate said that the training was organized to build the internal capacity of both the administration and academic staff of theTraining and Consultancy Service wing and to come up with new modalities in the new academic year.




In another development Training and Consultancy Service Coordination Directorate organized one day introductory training on theoretical and conceptual understanding on E-learning program for consultants and directors on September 19,2017 at Training Center.The training was organized with the objectives to capacitate the staff and be able to give a quality and standard training for traineesthrough E- learning programs and meet the growing demands for trainings. which in turn helps to make the center more accessible and competent training center.

It is learnt that the Training and Consultancy Service Coordination Directorate has planned to organize consecutive training programs for consultants and directors on different issues. The center also plans to deliver E-learning programs for the public service sector by this academic year.

## Gender and HIV/AIDS Affairs Directorate Gives Training

Ethiopian Civil Service University Gender and HIV/AIDS Affairs Directorate organized half day training for Training Facilities and Hospitality Services Coordination Directorate staff on 05 September 2017 at Hidasse Hall. The training was mainly focused on HIV/AIDS and related issues and life skills experiences.
W/ro Abay Akemachew Director for Gender and HIV/ AIDS Affairs Directorate on the training said the training was organized to create awareness and enable the trainees to enhance their level of knowledge about HIV/AIDS and life skills experiences. "From this training the trainees are expected to gain valuable ideas on issues like self awareness, effective communication, problem solving, critical thinking, interpersonal relationship, decision making and other issues. It also helps them to set their own future plan and lead their life in an appropriate manner" W/ro Abay noted.



The training was presented with explanations and group discussion methods to create good opportunities for the trainees to share their knowledge and life skill experiences among themselves.

The training was given by W/ro Abay Akemachew and about forty trainees recruited from Training Facilities and Hospitality Services Coordination Directorate participated.



Gender and HIV/AIDS Affairs Directorate has been giving consecutive trainings on HIV/AIDS, gender and other related issues and working to minimize HIV/ AIDS prevalence focusing on both ECSU staff members and students.

## EKI Hailed ECSU

Ethiopian Kaizen Institute awarded Ethiopian Civil Service University two teams and three best performing individuals for their excelled performance in implementation of kaizen philosophy in their respective directorate on October7, 2017 at Ghion Hotel.




Certificate of recognition and cup were awarded to Enat kaizen Practice Team and Simintu Kulifoch kaizen Practice Team and the winners of the KPT contest individuals: Ato Abel Taddese and Ato Abdurhaman Shemsedin in capacity building wing and W/ro. Zewidnesh Atinafu, who stood third from the individual contest conducted at the national level.

On the occasion, Ato Tagesse Chaffo, Minister for Ministry of Public Service and Human Resource Development congratulated all the institutions and best performing individuals for their remarkable achievements.



He also advised them to continue exerting their utmost efforts with the same spirit and try to achieve more results and step up their performance in the future.

Mr.Shinich Sada Japan ambassador to Ethiopia on his part expressed his pleasure by the result obtained in implementing kaizen in Ethiopia. He also assured that Japan continues its vibrant support for kaizen implementation in Ethiopia.

In related development, Ethiopian Civil Service University also organized a recognition program for the Enat KPT and Simintu Kulifoch KPT teams and winners in Kaizen practice contest on October 12, 2017 at Hidasse Hall.




Ato Ayneabeba Andualem, Director for Reform and Good Governnce Directorate briefed the participants

about the status of Kaizen implementation in the University.

On the program Professor Fikre Dessalegn, Ethiopian Civil Service University president, congratulated the winning teams and individuals for their excellent performances and advised them to exert a greater effort to continue as best team and make ECSU the best institution in kaizen practice.

Ato Mekonen Yaie, Director for Ethiopian Kaizen Institute, on his part congratulated ECSU for the achievement obtained and reminded the teams and winners of the Kaizen practice that kaizen is a global movement and an endless process. ECSU is one of the capacity building institutions in the country. It is expected from the institution to be exemplary in all aspects and fully engage in the movement to be center of excellence by the year 2017 in Kaizen practice too, said Ato Mekonen.

## ECSU Holds Community Service Consultation Workshop

Ethiopian Civil Service University held Research and Community Service consultation workshop with Federal and Regional stakeholders on October 6 2017 at Hidase Hall.



In his opening speech, Professor Fikre Dessalegn, Ethiopian Civil Service University president welcomed the stakeholders and mentioned the ECSU contribution in building the capacity of the public sector in teaching, training and consultancy and conducting researches on the demands of the public sector by its research and community service wing. He also mentioned that based on previously conducted Research and Community Service consultation workshop with stakeholders different research and consultancy services have been done on the identified thematic areas. From this workshop, we believe that different invaluable and constructive ideas will be raised for a better performance in the future and we can indentify important research thematic areas too., Professor Fikre Added.

Dr. Birhanu Belayneh, vice president for Research and Community Service, on his part welcomed the participants and underscored the importance of the roles that stakeholders



play for the successes of higher education institutions to achieve their goals. With this spirit ECSU by the last academic year conducted the consultation workshop.



Based on the input obtained from the workshop, different progresses have been made in research and community service as well as in the teaching learning process. It is also believed that some additional inputs will be obtained from this workshop, Dr. Birhanu added.

On the program an overview of the Ethiopian Civil Service University Research and Community Service activities that have been done since its establishment were presented by Dr.Mekonen Kassahun, Director forCenter for Research in Public Service Reforms. In addition presentations on ECSU research activities and outcomes, community service engagements and university industry linkage aspects were presented by ECSU scholars.

The participants on their part expressed their pleasure for taking part on the consultation workshop and raised different comments and ideas and the house thoroughly discussed on them

# የግንባር ቀደሞች እውቅና

በአገራችን የፐብሊክ ሴክተሩን ብቃትና ውጤታማነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የተለያዩ የለውጥ መሳሪያዎች ሲተገበሩ ቆይተዋል፡፡ እነዚህ የለውጥ መሳሪያዎች ተቋማዊ ለውጥን በማረጋገጥና ተቋማዊ ተልዕኮን በውጤታማነት በመፈጸም የህዝብ እርካታን ለማስመዝገብ ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም የተቋማዊ ለውጥ ትግበራውን የበለጠ ለማጎልበት እነዚህን የለውጥ መሳሪያዎች ተጠቅሞ ውጤት እያስመዘገበ፣ የተመዘገቡ ውጤቶችም መሰረት በማድረግ ለበለጠ የስራ አፈጻጸም የሚተጋ የፐብሊክ ሰርቪስ የለውጥ ሰራዊት በማደራጀትና ወደ ስራ በማስገባት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት የተጀመረውን የለውጥ ስራ እያጠናከሩ ለመሄድ በማንኛውም የስራ እርከን ላይ የሚገኙ አካላት በሙሉ በመተባበር፣ በመቀናጀትና ለውጡን መሰረት በማድረግ የልማትና የመልካም አስተዳደር እቅዶችን በቅልጥፍናና በውጤታማነት ለመፈጸምና የጋራ ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚያስችል የለውጥ ሰራዊት መገንባት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

የለውጥ ሰራዊት ገንብቶ መንቀሳቀስ ከሚኖረው ፋይዳ ውስጥ በተቋማዊ ለውጡ አማካኝነት የተፈጠረውን አደረጃጀትና አሰራር በመጠቀም ውጤት እንዲያመጣ የሚፈለገው የሰው ኃይል በአመለካከቱ አዎንታዊ ለውጥ በማምጣት የፈጣን ልማትን ቀጣይነት እንዲኖረው የድርሻውን እንዲወጣ ማድረግ አንዱና ዋነኛ ሲሆን የለውጥ ሰራዊት መገንባት በየደረጃው በሚገኙት የሰራዊት ክንፎችና አካላት መካከል የአመለካከትና የተግባር አንድነት እንዲፈጠር ለማድረግ፣ የቡድን መንፈስን ለማዳበር፣ የሰራዊቱን አቅም ለማመጣጠን፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን በፍጥነት ለማስፋትና የፐብሊክ ሰርቪሱን የእርስ በርስ መማማር ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ለመገንባት ተኪ የሌለው ሚና ይጫወታል፡፡ በለውጥ ሰራዊት አግባብም ከሰራዊቱ አባላት መካከል የለውጥ መሳሪያዎች አስተሳሰሮ ከመፈጸምና አርአያ ሆኖ ከመገኘት እንዲሁም የላቀ አፈጻጸም ከማበርከት አንጻር ግንባር ቀደም የሆኑትን በመለየት ለቀጣይ ተግባራት በሌሎች ሰራተኞች ዘንድ ተነሳሽነትን በመፍጠር ለተቋማዊ ስኬት መነቃቃትን ለመፍጠር የእውቅና አሰጣጥ ሥርዓት ይከናወናል፡፡ በግንባር ቀደምነት የሚለየውም አካል የራሱን ተልዕኮ በብቃት በመፈፀምና የተቀመጠውን ግብ በላቀ ሁኔታ ያሳካ፣ ሌሎች ሰራተኞችንም እርሱ በደረሰበት የአመለካከት እና የአፈጻፀም ደረጃ እንዲደርሱ በማገዝና ልምዱን በማካፈል ሌሎችም በአመለካከት፣ በክህሎትና በዕውቀት ያለባቸውን ክፍተት ለመሙላት ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ፣ ለውጥ የሚያመጡ አዳዲስ አሰራሮችን ማመንጨትና ለሌሎችም ምሳሌ በመሆን የተቋማዊ ተልዕኮ ውጤታማነት ስለሚሳካበት ሁኔታ በመርህ ላይ ተመስርቶ በመተባበርና በመተጋገዝ በመስራት፣ መልካም ስነ-ምግባር ያለው፣ ታታሪ እና ስራ ወዳድነትን የተላበሰ መሆን ይገባዋል፡ ፡በዚህ መርህ ላይ በመመስረትም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ በ2009 በበጀት ዓመት የለውጥ ሠራዊትን በተጠናከረ መልኩ ለማስኬድ በመምህራን፣ የአስተዳደር ሰራተኞችና በተማሪዎች በአጠቃላይ 694 የ1ለ5 ቡድኖች ተደራጅተው ስራን በጋራ የመምራት፣ መከታተልና መገምገም ፣ ችግሮችን በወቅቱ የመለየትና መፍትሄ የመስጠት ፣ የእርስ በርስ የመማማርና አቅም መገነባበት እና የመሳሰሉት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በእነዚህ የለውጥ ሰራዊት አደረጃጀቶችም በየዘርፉ የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ ግንባር ቀደም ፈጻሚዎችና ዳይሬክተሮች መስከረም 08 ቀን 2010 ዓ.ም የእውቅና አሰጣጥ ስርዓት ተከናውኗል፡፡

ግንባር ቀደሞቹም የተለዩበት መስፈርትም በለውጥ ሰራዊት ማንዋል በተቀመጡት የመለያ መስፈርቶች አማካይነት 5 ፐርሰንት የማይበልጡ ግንባር ቀደሞችና ኃላፊዎችን በመለየት እንዲያቀርቡ በዘርፍ በተላከው መስፈርት መሰረት የቀረበውም ዝርዝር በተቀመጡት መስፈርቶች አሰራሩን ተከትሎ የተከናወነ መሆኑን የዕቅድ ሰነዶችን፣ ቃለ ጉባኤዎችና ሌሎች ሰነዶችን በመገምገምና በማረጋገጥ ከቀረቡት እጩዎች መካከል ከ5 ፐርሰንት የማይበልጡትን ግንባር ቀደሞችንና ኃላፊዎች በመለየት ለዩኒቨርስቲው ማኔጅመንት በማቅረብ መሆኑን ከለውጥና መልካም አስተዳደር ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡



ከእነዚህ ግንባር ቀደም ሰራተኞች መካከልም የጥቂት ግንባር ቀደሞች የስራ ባህልና መልካም ተሞክሮ ለሌሎች ማነቃቂያ ይሆን ዘንድ እንደሚከተለው ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡
የመጀመሪያና በበጀት ዓመቱ ብቸኛ የዋንጫ ተሸላሚ የሆኑት የስልጠና ፋሲሊቲና መስተንግዶ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሆኑት አቶ ሽሪፍ ሙዘይን ናቸው፡፡

አቶ ሸሪፍ ሙዘይን በተቋሙ ለአስራ ሁለት ዓመታት አገልግለዋል፡፡ ባላቸው ከፍተኛ የሥራ ባህል ከሥራ ክፍላቸው ባሻገር የዩኒቨርሲቲውን መልካም ገጽታ በመገንባት ሂደት ላይ ቁልፍ ሚና ከሚጨወቱት አካላት የመጀመሪያውና ግንባር ቀደም ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡ በክፍላቸው ጠንካራ የሆነ የለውጥ ሰራዊት እንቅስቃሴ መኖሩን የሚገልጹት አቶ ሸሪፍ የለውጥ ሰራዊትን እንደታላቅ የሥራና የአንድነት ስሜት መፈጠሪያ መድረክ እንደሚጠቀሙበት፣ የተቆርቋሪነትና የኃላፊነት ስሜት ማዳበሪያ አንዱ መሳሪያ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ በክፍሉ የሚገኙት ከሁለት መቶ በላይ ቋሚና ከአንድ መቶ በላይ ጊዜአዊ ሰራተኞች በዚሁ የለውጥ ሰራዊት አደረጃጀት ታቅፈዋል፡፡ በአንድ ለአምስት በመገናኘትም የዕለት ውሎ ተግባራትን ይገመግማሉ፡፡ በሶስት ቡድን ተደራጅተውም በየሳምንቱም በመገናኘት አጠቃላይ ወይይት የሚደረግበት ሥርዓት በክፍሉ ዘርግተዋል፡፡



የተገኘውም ሽልማት በአጠቃላይ በክፍሉ ያለው ሰራተኛ በዚህ በለውጥ ሰራዊት አገባብ በተዘረጋው ወጥ የሆነ ሥርዓት ተደራጅቶ በትጋት በመሥራቱ ነው፡፡ ይህም በተቋሙ ማህበረሰብ ዘንድ እንደ አርአያ እንድንታይ አስችሎናል የሚሉት አቶ ሸሪፍ በዋናነት ለዚህ ደረጃ ያበቃቸው በክፍሉ በሰራተኞቻቸው ዘንድ የአመለካከት ለውጥ መፍጠር ላይ የሰሩት ሥራ እንደሆነና ሠራተኞችን በአግባቡ ለመቅረጽ የተሰራው ስራም ፍሬን በማፍራቱ መሆኑን እንደሚያምኑ ለዝግጅት ክፍሉ አሰረድተዋል፡፡
“ሰራተኞች በሚከፈላቸው ገንዘብ ሳይሆን በሚሰጡት አገልግሎት ተገልጋይን በማርካት ከሚገኝ የደስታ መንፈስን ለመፍጠር ነው ስተጋ የነበረው፣ ለዚህም ብዙ ደክሚያለሁ፡፡ በመጨረሻም ውጤት አግኝቼበታለሁ፡፡ አሰራራችንም በዚህ መንፈስ የተቃኘ በመሆኑ አዳዲስ ሰራተኞች እንኳን ወደክፍሉ ሲመጡ በዚሁ በተዘረጋው መስመር ነው ሥራቸውን የሚከናወኑት፡፡ እኛ ጋር ደንበኛ ንጉስ ብቻ ሳይሆን ከንጉስም በላይ ነው፡፡ ተገልጋይ ሲደሰት እኛም እንደሰታለን፡፡ ለመገልገል የመጣ ደንበኛ በምንም ምክንያት አዝኖና ተከፍቶ መመለስ የለበትም፡፡ በእኛ አቅም ሊቃለል በሚችል ነገር በፍጹም የቅሬታ ምንጭ መሆን የለበትም የሚል አመለካከት ባለው ሰራተኛ ዘንድ እንዲሰርጽ ነው የሰራነው፡፡ እኔም በተቻለኝ አቅም ሁሉ የሞራል ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም አሰራሮችን በመከታተልና ተገቢውን ድጋፍ በመስጠት እንደ አንድ ሆነን ስራችንን በተገቢው ሁኔታ በማከናወን ላይ እንገኛለን፡፡ ቅዳሜ እና እሁድን እንዲሁም የበኣላት ቀንን ጨምሮ ከስራ ሰዓት ውጪም በስራ ገበታ ላይ እንገኛለን፡፡ በዚህም የዩኒቨርስቲው አመራርና የመላው የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ድጋፍ ታክሎበት ደንበኞቻችንን በሚገባ ሁኔታ ለማርካት ችለናል ብዬ አስባለሁ፡፡ ” ብለዋል፡፡

በማስከተልም ስራን አስመልክቶ ያላቸው አቋም ሲያብራሩ ሥራን ከልባቸው አጥብቀው እንደሚወዱ፣ ሰራተኞቹም ስራን ከልባቸው መውደድ እንዳለባቸው ምክራቸውን ዘወትር እንደሚለግሱ ገልጸዋል፡፡ በአጠቃላይ በማንኛውም ዘርፍ የደከመና መስተካከል የሚገባው ነገር ካለ በዝምታ ማለፍን አይወዱም፡፡ የሕይወት መርሀቸውም ሥራ ብቻ ነው፡፡ ስራ አድክሞኝ አያውቅም የሚሉት አቶ ሸሪፍ ውጤት ለማስመዝገብና ተገልጋዮቼን እስከማረካ ድረስ በማንኛውም ጊዜና ሰዓኣት ሁሉ እሰራለሁ፡፡ በስራ ላይ ምን ቸገረኝ እና የእኔ ድርሻ አይደለም የሚል አመለካከት ፈጽሞ የለኝም፡፡ ነገሮችንም እስከመጨረሻው ድረስ በመሄድ ተከታትዬ አንዳች ውጤት ካላመጣሁ እረፍት የለኝም ብለዋል፡፡ በዕለት ስራቸው ላይ የጎደለ ነገር እንዳለ ከተሰማቸውም ሌሊት እንቅልፍ እንደማይኖራቸው፤ ቤታቸውም ሆነው ስለ ቀጣዩ ቀን የስራ ሁኔታ እንደሚያስቡ፤ የክፍሉ ሰራተኞችም እንዲሁ ለስራ እንደሚተጉ ገልጸዋል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው ሰራተኞቹን በማሳመን እንደሆነና ሌሎችም ይህን ቢከተሉ ውጤታማ እንደሚሆኑ ይመክራሉ፡፡ ከዘንድሮ ዓመት ተሸላሚዎች መካከልም በአብዛኛው ቀድሞ በስልጠና ፋሲሊቲና መስተንግዶ ዳይሬክቶሬት ክፍል ይሰሩ የነበሩና በዝውውር ወደሌላ ክፍል የተዘዋወሩ መሆናቸውን በመግለጽ በዚህ በክፍላችን ምን ያህል ጠንካራ የስራ ባህል እንደነበር የሚያሳይ እንደሆነ በመሸለማቸውም እጅግ በጣም ደስተኛ እንደሆኑ እንዲሁም ዘንድሮ በተከታታይ ለሶስተኛ ጊዜ ያገኙት ሽልማት በቀጣዩ ዓመትም ለአራተኛ ጊዜ እንደሚደገም ያለአንዳች ጥርጣሬ በቁርጠኝነት ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ ለሶተኛ ጊዜ ተሸላሚ የሆኑት በዲቨሎፕመንት ኢኮኖሚክስና ማኔጅመንት ዲፓርትመንት መምህር አቶ ኪዳነማርያም ግደይ ናቸው፡፡ በዩኒቨርስቲው ለአራት ዓመታት አገልግለዋል፡፡

ከመጀመሪያው ዓመት ባሻገር በተቀሩት ሶስት ተከታታይ ዓመታት በግንባር ቀደምነት ተሸልመዋል፡፡ በዲፓርትመንታቸው ያለው የለውጥ ሰራዊት እንቅስቃሴም በጥሩ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ እንቅስቃሴውም በዕቅድ እንደሚመራና እቅዱን መሰረት በማድረግ በየወሩና በየሳምንቱ በመገናኘት ክትትልና ግምገማ እንደሚደረግ አስረድተዋል፡፡ በዚህ እንቅስቃሴም እስከ ግለሰብ ወርዶ በሚዘጋጀው ዕቅድ መሰረት ከመማር ማስተማሩም ባሻገር የምርምሩና የማማከሩን ተግባራትንም በዕቅዳቸው ውስጥ በማስገባት በተቻለ መጠን ያንን ዕቅድ ለማሳካት ጥረት ያደርጋሉ፡፡

ከሌላው የአካዳሚክ ሰራተኞች የተለየሁ ነኝ ለማለት ባልደፍርም ለስራዬ በጣም ተገዢ ነኝ የሚሉት አቶ ኪዳነማርያም የሚጠበቅብኝ የሚሉትን ስራ በአግባቡ እና በሰዓቱ ካላከናወኑ ጥሩ ስሜት እንደማይሰማቸው፣ ይህም በተፈጥሮ የተቸረኝ ስጦታ ነው ብለው እንደሚያምኑ ገልጸዋል፡፡ በዕቅዳቸው ያሰፈሯቸውን ተግባራት ለማከናወን ዘወትር ከሚያደርጉት ጥረት ባሻገር ተማሪዎችን ለማገዝ በየዓመቱ የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች አሉ፡፡



ይህንም ‹‹የዲቨሎፐመንት ኢኮኖሚክስና ማኔጅመንት ዲፓርትመንት ተመራቂ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሑፍ ሲያዘጋጁ የሚጠቀሙት ስታስቲካል ፓኬጅ ሶፍት ዌር በየዓመቱ ለተማሪዎች በነጻ እሰጣለሁ፡፡ የተለየ የምለው እንቅስቃሴ ይህ ነው ፡፡ በዚህም ተማሪዎቹን በአቅሜ በመርዳት ላይ እገኛለሁ፡፡ በዩኒቨርስቲው ደረጃ ባለው የምርምር ስራ ላይም በንቃት እሳተፋለሁ፡፡ በእነዚህና በመሳሰሉት አገልግሎቴ ነው ለእውቅና የበቃሁት ለሁሉም ነገር መነሻውና ቁልፉ ጉዳይ ግን በተፈጥሮዬ ያለኝ የስራ ፍቅር ነው ለማለት እችላለሁ፡፡›› ብለዋል፡፡


በለውጥ ሰራዊት ቡድኖች መካከል በሚደረጉት ስብሰባዎች የአንደኛውን ምርጥ ተሞክሮ ለሌላው የማስተላለፍ ሁኔታ አለ፡፡ ሀሳቦችን የመጋራት ሁኔታው እንደተጠበቀ ሆኖ ሂደቱ ግን መደበኛ ስርዓት የተከተለ ባለመሆኑ የራሱ የሆነ ክፍተት እንዳለው ይታመናል፡፡

በእያንዳንዱ የለውጥ ሰራዊት ያለን መልካም ተሞክሮ ለሌላው ለማስተላለፍ ዩኒቨርስቲው ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደአለበት ያላቸውን አስተያየትም ለግሰዋል፡፡

ሌሎች ሰዎች ከእርሳቸው መማር ስለሚገባቸው ነገር ሲገልጹ ሰው ለስራው ተገዢ መሆን እንደአለበትና አላማም ሊኖረው እንደሚገባ፣ ሰውን የሚለወጠውም በስራ ብቻ ነው ብለው እንደሚያምኑ አስረድተዋል፡፡ በማንበብና የሌሎችንም ተሞክሮ በመውሰድ ሰዎች ራሳቸውን መለወጥ አለባቸው፡፡ ራስን ለመለወጥ ዓላማ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ብዙ ነገር በማድረግ ራስን መለወጥ ሲቻል ጊዜአቸውን አለአግባብ የሚያባክኑ ግለሰቦች አሉ፡፡ ያለስራ መለወጥ አይቻልም፡፡ ሰው ራሱንም ቤተሰቡንም ሀገሩንም መለወጥ የሚችለው በስራ ብቻ ነው የሚል ምክራቸውን ለግሰዋል፡፡

በተማሪዎች ዘንድ ስላለው የለውጥ ሰራዊት እንቅስቃሴም የተማሪዎችን የለውጥ ሰራዊት አደረጃጀት ብዙ ነገር ይቀረዋል ፡፡ ተማሪዎች የለውጥ ሰራዊቱን አላማ በመገንዘብና በአግባቡ በመጠቀሙ ረገድ ጠንካራ ስራ መሰራት አለበት፡፡ አደረጃጀቱ አለ፣ ነገር ግን እርስ በርስ ለመረዳዳት ብዙ እየተጠቀሙበት አይደለም፡፡ በዩኒቨርስቲ ደረጃ ብዙ መሰራት አለበት የሚል አስተያየታቸውን ለግሰዋል፡፡

ሌላዋ የዓመቱ ግንባር ቀደም ተሸላሚ የሆነችው ወይዘሪት ዓለምነሽ አስፋው ከተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት አስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ቡድን ክፍል ሰራተኛ ስትሆን የግንባር ቀደም ፈጻሚ ተብላ ስትሸለም ይህ ሁለተኛ ጊዜዋ ነው፡፡



ሁሌም በእቅድ በመመራትና በክፍሉ ውስጥ የድርሻዋን ለመወጣት በትጋት እንደምትሰራ የምትገልጸው ወ/ት ዓለምነሽ ስራዎች በታቀዱት መሰረት መከናወናቸውን ክትትል በማድረግ ምንም ዓይነት የስራ ክፍተት ሳይከሰት ተማሪዎች ከክፍሉ ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎት በተገቢው ሁኔታ እንዲያገኙ ከክፍሉ ሰራተኞች ጋር በጋራ በመሆን ስራዎችን በመስራት ላይ መሆናቸውን ትጠቅሳለች፡፡ በየሳምንቱ በዕቅዳቸው መሰረት የተከናወኑ ተግባራትን አፈጻጸማቸውን በመገምገም ያልተሰሩ ተግባራትን ደግሞ ለይቶ በመያዝና የሚፈጸሙበትን ስልት በመቀየስ ስራው በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲፈጸም ዘወትር ትተጋለች፡፡

በዘንድሮው አመት ተሸላሚ እንድትሆን ያስቻላት የተለየ ተግባር ምን እንደሆነ ተጠይቃ ስትመልስም “ለዚህ ሽልማት ያበቃኝና ከሌሎች የተለየም ባይሆን በግንባር ቀደምትነት እንድመረጥ ያስቻለኝ የምለው ነገር ለስራ ያለኝ ፍቅር ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ሁሌም የምሰራው ለህሊናዬ ነው፡፡ ሰው እንዲያየው ወይም በአለቆቼ ለመወደስ በማለት የማደርገው አንዳች ነገር የለም፡፡ የእኔ  አለቃ ስራዬ ነው፡ ስራዬን ሁሌም አከብራለሁ፡፡” በማለት ገልጻለች፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ባለፉት አስር ወራት ለክፍሉ  በቂ ሰራተኛ ባለመመደቡ በነበረው ክፍተት ሠራተኞች እስኪመደቡ ድረስ የአራት ሰዎችን ስራ ደርባ በማገልገል ላይ መቆየቷ በማስታወስ  በወቅቱም በነበረው የሰው ኃይል እጥረት ምክንያት ምንም ዓይነት የስራ  ክፍተት ሳይኖር የዓመቱን እቅድ ለማከናወን መቻሉ በግንባር ቀደምነት ለመመረጥ እንዳስቻላትም ጠቁማለች፡፡


ስለቀጣይ ዕቅዷም ስትገልጽ በቀጣይም ከዚህ የበለጠ በትጋት ለመስራት እና የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ ጠንክራ እንደምትሰራ ፤ሌሎችንም ለማብቃት በሚደረገው ጥረት በክፍሉ አዲስ የተመደቡ ሰራተኞችን በዩኒቨርስቲውና በዳይሬክቶሬቱ ያለውን የስራ ድባብ ከማለማመድ አንስቶ በሚያስፈልጋቸው ሁሉ የሚጠበቅብኝን በማረግ ሁሉም የክፍሉ ባልደረቦች ወደ ላቀ የስራ አፈጻጸም ደረጃ እንዲበቁ ብሎም በርካታ ግንባር ቀደም ሰራተኞችን ለማፍራት ሁሌም እንደምትሰራና  በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ከጎናቸው መሆኗንም፤  ይህ ተግባሯም ወደፊት ተጠናክሮ የሚቀጥል እንደሆነ ትገልጻለች፡፡ በእሯሷ ዕውቅና ማግኘት በመነሳትም በክፍሉ ጥሩ የስራ መነቃቃት ፤ከፍተኛ የሆነ የሞራል መነሳሳትና የቡድን መንፈስ በመፈጠሩ በቀጣዩ ዓመት ከፍተኛ ውጤት እናስመዘግባለን፤ በርካታ ግንባር ቀደሞችንም እናፈራለን ብዬ አስባለሁ በማለት ሀሳቧን ገልጻለች፡፡
ሌላዋ ግንባር ቀደም ወ/ሮ ተናኜ ኃይሉ የዩኒቨርስቲው ካምፓስ ፖሊስ በመሆን በዩኒቨርስቲው ለአራት ዓመታት አገልግላለች፡፡
በስራ ላይ ሁሌም በትጋት መስራት እንዳለባት የምትገልጸው ወ/ሮ ተናኜ ከባልደረቦቿም ጋር በመተባበርና እርስ በርስ በመረዳዳት እንደምትሰራ የተጣለባትንም ኃላፊነት ለመወጣት በትጋት መስራት እንዳለባት ከልቧ ታምናለች፡፡
ከባልደረቦቿ ጋር ባላት ማህበራዊ ግንኙነት ጠንካራ መሆኑን የምትገልጸው ወ/ሮ ተናኜ ስራና የግል ግንኙነት የተለያየዩ መሆናቸውንና ከማንኛውም ነገር በፊት ለስራ ቅድሚያ እንደምትሰጥ ትናገራለች፡፡ እንደ ክፍልም በየእለቱ በምናከናውናቸው ተግባራት እና አልፎ አልፎ  ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመቅረፍ በጋራና ግልጽ በሆነ ሁኔታ በመመካከርና ችግሮችን ከምንጫቸው ለማክሰም ፣ በስራችንም ክፍተት እንዳይታይ ተግተን እንሰራለን፡፡ እንግዶችን ተገቢውን ክብር በመስጠት በዩኒቨርስቲው የሚፈልጉትን አገልግሎት በአግባቡ አግኝተውና ተስተናግደው የዩኒቨርስቲውም ደህንነት በአግባቡ ሲጠበቅ ማየት የክፍሉ ሰራተኞች ተቀዳሚ ዓላማና ፍላጎት በመሆኑ እርሷም ይህን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት በትጋት እንደምትሰራ ትገልጻለች፡፡



ለሽልማት ያበቃት ነገር ምን እንደሆነ ተጠይቃ ስትምልስም “ስራዬን በጣም እወዳደዋለሁ፡፡ ሁሌም  የምሰራውም በደስታ ነው፡፡ ዘወትር ወደ ዩኒቨርስቲው በጠዋት በመምጣት በስራ ምድቤ ላይ በሰዓቱ እገኛለሁ፡፡ ሥራዬንም በጥንቃቄ በመስራት ያለ አንዳች ክፍተት በየዕለቱ የሚኖርብኝን የዕለት ተግባሬን አከናውናለሁ፡፡ በክፍሉ ባለነው ሰራተኞት በአብዛኛው የሚደረግ የዘወትር ተግባር ነው፡፡ ሁላችንም እርስ በርስ ሀሳብ በመስጠት እየተገነባባን እንሄዳለን፡፡ ያለ አንዳች መሸፋፈን ያለውን ጠንካራና ደካማ ጎናችንን በመነጋገር መታረም በሚገባቸው ጉዳዮችን በማረም ስራችችንን እናከናውናለን፡፡ ግንባር ቀደም የመሆን ጉዳይ ከመካከል ነጥሮ የመውጣት ጉዳይ ነው እንጂ ሁሉም በትጋት ነው የሚሰራው፡፡” ብላለች፡፡ ሽልማቱም የበለጠ መነሳሳትን በእኔም በባልደረቦቼም ላይ የፈጠረ በመሆኑ ለወደፊትም ከእኔ የበለጠ ተግባር የሚያከናውኑ የስራ ባልደረቦቼ እንደሚኖሩ አልጠራጠርም፡፡ እኔም በዚሁ ቁርጠኛ አቋሜ ስራዬን የምቀጥል ይሆናል በማለት ሀሳቧን ቋጭታለች፡፡

ውድ አንባቢያን በለውጥ ሰራዊት አግባብ በመንቀሳቀስ የተቋምን ግብ ብሎም ሀገራዊ ራእይን ማሳካት እንደሚቻል ከላይ ለአብነት ያቀረብናቸው ተሸላሚዎች የስራ ተሞክሮ በተገቢው የሚሳይ ነው፡፡ ከነዚህ ተሞክሮዎች ተነስተን ሁላችንም ግንባር ቀደም በመሆን የዩኒቨርሲቲያችንን ራእይ በማሳካት ሀገራችን የተያዘችውን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ የመሰለፍ ራእይ ለማሳካት እንረባረብ የሚለው የዛሬው መልክታችን ነው፡፡

# ECSU_Sattelite Road Map





ሲቪል ሰርቪስ ኤፍ.ኤም. 100.5
የማኅበረሰቡ ድምጽ!
100.5
በFM 100.5 ሜጋ ኸርዝ
ዘወትር ከጠዋቱ 3:00 እስከ ቀኑ 8:00 ሰዓት ድረስ
ጣቢያችን በማኅበረሰባችን ተሳትፎ ማኅበረሰቡን የሚያገለግል የማኅበረሰብ ድምጽ ነው።
የሴቶች ፕሮግራም
ጥናትና ምርምር
ጤና
በመልካም አስተዳደር ጉዳይ
ስፖርት
የማኅበረሰቡ ጉዳይ መሳ መፍጠሪያ
ባህልና
ሌሎች ፕሮግራሞችን አካተን ማኅበረሰባችንን
እያገለገልን ነው። እርሶም ይሳተፉበት!
ዩኒቨርሲቲያችንነ ማስተዋወቅ
የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን
ቋንቋ ፣ ባህልና ጥበብ ማስተዋወቅ፤
የሃገራችንን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እና
ሌሎች ዕቅዶች እንዲሳኩ የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ማስፋት፤
ማኅበረሰቡን መሰረት ያደረጉ የመዝናኛ ፕሮግራሞችን
በማዘጋጀት እያዝናኑ ማስተማር፤
በዩኒቨርሲቲያችን እንቅስቃሴዎች እንዲሁም በዓለማቀፍ ጉዳዮች
ላይ ማኅበረሰቡ ተገቢና ትክክለኛ መረጃ እንዲኖረው ማድረግ፤
የማኅበረሰቡን ገንቢ ተሳትፎ በማጠናከር ለፖለቲካዊ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያና ባህላዊ ዕድገት
ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ፕሮግራሞችን ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ ነው።
Contact us
0116-67-54-71/0116-67-55-06
ሞባይል፡ 0930-59-81-26
(ለጽሁፍ መልዕክት ብቻ)
ፋክስ፡- 0116-46 30 16
ፌስ ቡክ፡-FM100.5
fm100.5ecsu@gmail.com
ድረ ገጽ፡-www.ecsu.edu.et
ፖ.ሳ.ቁ.፡-5648
የኢትዮጵያ ሲቭል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የማኅበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያ